## ያገር ያለህ!

# “አለ ነገር ይስማው አገር!!!”

## ኢትዮጵያን ከካርታ ህዝቡአን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት በእናት ሃገራችሁ ማሕጸን ላይ አፍጥጣችሁ የባእዳን ሎሌ ሆናችሁ በ80 ሚሊዮን ህዝባችን ህይወት ላይ እየፈረዳቹ ላላችሁ ሁሉ።

የኢትዮጵያን ሃገራዊ ጦር በትናችሁ፡ ኤርትራን ከእናት ሃገሩአ ገንጥላችሁ የባህር በሮቻችንን ለመንገደኛ ባዒድ የጦር አውራ ጎዳና አድርጋችሁ ከ70 ዓመት በፊት ጣሊያን ያቀደልንን የመከፋፈያ የክልል ካርታ ሳትመረምሩ እንተገብራለን ብላቹ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለሚተላለፍ የቂም ቁርሾ አስቅጥራቹ ከአንዱ ክልል ሃገር ቆርሳቹ ከሌላውም ለም መሬት ቆንጥራቹ ላንዱ እየደጎሳቹ የለለብንን የጎሳ ኩፈሳ ፈጥራችሁልን አፋጣችሁን ላላቹ የወገን ጠላቶቻችን ሆይ!

- ተቃዋሚዎችን ለ17 ዓመት ትግራይ ጉድጉአድ ላጎራቹ
- ጎንደር ዓደባባይ ኢየሱስ ቤ/ክርስቲያን በምህላ ላይ ባሉ ወገኖቻችን ላይ እደጀ ሠላም ውስጥ ጨፍጭፋቹ
- አንዋር መስጊድ ተሳላሚ በሆኑ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ዜጎቻችንን እረምርማቹ
- የ ኤርትራን ክ/ሃገር አትገነጠልም በማለት ሰላማዊ ሠልፍ የወጡ የነገ ተስፋዎቻችን በሻጋታ ቢላዋ አንጀት እና ማህጸናቸውን ዘረጋግፋቹ (በዩኒቨርሲቲ)
- የወላይታ ገበያተኞችን አረካ ላይ በቦምብ አጋይታቹ
- ዘምባባ በያዙ ሲዳማዎችን አዋሳ መግቢያ ላይ ጠብቃቹ 300ውን ረፍርፋቹ
- ኤሊባቡር ተፒ መሬቱን ለቱጃር ለመሸጥ 1300 ንፁሃንን እንደድኩላ እያሳደዳቹ ገላቹ
- ለሙ የኢትዮጵያን ምድር ጋምቤላን ለማሌዥያ ቱጃሮች ለመሸጥ ስትስማሙ ተቃውሞ ስላሰማ ከሺህ በላይ አኝዋኮችን አኝካችሁ በልታችሁ
- በቅጥረኝነት ሶማሌ ውስጥ ገብታችሁ ሕጻናትንና ሼካዎችን መስጊድ ውስጥ እያረዳቹ ለነገዋ ኢትዮጵያ የወንጀልና የቂም ዕዳ እያከማቻችሁ
- ኦጋዴንን ለማስገንጠል ምቹ ሁኔታን እያመቻችሁ ባለበት
- የኢትዮጵያ ምሁራንን አማራ በሚል ታፔላ የዘር ቁርሾአችሁ እያቀረሻችሁ ከስራ እየፈነገላችሁ ያስተማራቸውን ድሃ ሃገራቸውን እንዳያገለግሉ በሰበብ አስባቡ እያሳደዳችሁት ባለበት

# ያገር ያለህ!

- ትግራይ የኢትዮጵያስ አካል መሆኑአን ትታችሁ መላ ኢትዮጵያን ለጥቂት የአድዋ ባላባቶች ምርኮ አስገብታችሁ
- የደለበ የኢትዮጵያን ሃብት በባእድ አማካሪዎቻችሁ ቀጥተኛ የጌታ ትእዛዝ ተነሳስታችሁ 40 በማይሞሉ የትግራይ “ኢሊቶች” ጭራቅ ኩባኒያ አማካይነት ዛሬ የኢትዮጵያ እናቶችን የሊጥ ቡሃቃ ባዶ አድርጋችሁ እናንተ በጥጋብ ሕዝቡ በጠኔ ባለበት ሠዓት
- በ1997 ምርጫ በዜሮ ተሸንፋችሁ ድምጽ የነፈጋችሁን ሕዝብ ጨፍጭፋችሁ መልሳችሁ ባለማፈር ያሸነፋችሁን ወደ ትቢያ እናንተ የተሸነፋችሁት ስልጣኑን ነክሳችሁ ያልመረጣችሁንና ድምጼ አይቀማም ያለውን በወያኔ አርነት ትግራይ ተስፈንጣሪ አልሞ ተኩአሽ አርዳችሁ ጥላችሁ
  ይሄን እና ይሄን የመሳሰሉ ሺ ግብረ ወያኔ መዘርዝር ቢቻልም ወደ ዛሬ አመጣጣችን ስንመለስ ኢትዮጵያን አጥፍታችሁ ለመጥፋት ለተነሳችሁ ወያኔና የወያኔ ጉጂሌዎች ሆይ!
- የጎንደርን ለም መሬት ሁመራ-ወልቃይት-ጠግዴን ሂሳብ ሳታወራርዱ እንደገና የጎንደር ክ/ሃገርን 600 ኪ/ሜትር ከዳሎል እስከ ነፍሰ-ገቢ ተብሎ እስከሚጠራው
- ከነፍሰ-ገቢ እስከ ጋምቤላ 1000 ኪ/ሜትር ለም መሬት በድምሩ 1600 ኪ/ሜትር ርዝመት ወደ ጎን ደግሞ ከ 61 ኪ/ሜትር የሚበልጥ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊያጠግብ የሚችል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፍ የሚችል የነዳጅ እና የመዐድን ጎተራ የሆነ መሬት ለሱዳን ሸጣችሁ ከቋአራና አካባቢው 30 የሚጠጉ ከአርማጭሆና አካባቢው ከ800 በላይ ዜጎችን እንደ ባሪያ ፈንጋይ ምርኮኛ አድርጋችሁ ለባዕዳን ሰጣችሁ

ነገ ደግሞ ምን ታደርጉ ይሆን? እንጠብቃለን
ዛሬ ልናሳውቃችሁ መጣን እንጂ! ! !
ተጠያቂ መሆናችሁን ልንነግርአችሁ መጣን እንጂ! ! !
ከእናንተ ፍትህ መጠበቅ
ከእናንተ ዕውነት መጠበቅ
ከእናንተ ኢትዮጵያዊነት መጠበቅ
ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ይሻላል ካልን ሰንብተናል!!!!

# ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራልች

# አንድነታችንን በትግላችን እናስከብራለን

## የሀቀኛ ተቃዋሚዎች አንድነት ይጠነክራል! ወያኔም ይወገዳል!!